ታህሣሥ 24 ቀን 2003 ዓ.ም

# ወያኔ የደርግ ባለሥልጣኖችን "በምህረት" ሊለቅ ነው! የሰሞኑ አነጋጋሪ ዜና

# ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮኃል!

**ከአያልነሽ**

**በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈፀመው የሽብርና የግፍ ታሪክ _በአንድ መጽሐፍ ቅፅ ተወስቶ የሚያልቅ አይደለም። የኢትዮጵያ መንግሥት (ደርግ/ኢሠፓ) "ቀይ ትርዒት" ብሎ መጥራቱን የመረጠው ያ ሽበር፣ ጥሎ ያለፈውን የሕሊና ቁስልና በልዩ ልዩ ገፅታው ያስከተለውን መዘዝ ተንትኖ ለማቅረብ፣ እንዲሁም በዓይነ ምሥክር የተደገፉ ልዩ ልዩ መረጃዎችን ለማጠናከር አያሌ የመፅሐፍት ቅፆች ይጠይቃል።**

## (አንድ ትውልድ ለመምተር ቀዩ ሽብር በኢትዮጵያ! ባቢሌ ቶላ ከፃፈው የተወሰደ)

ሰሞኑን አገር አጥፊው አገዛዝና የዚህ ቡድን ፈላጭ ቆራጭ የሆነው ለገሠ ዜናዊ፣ የደርግ ባለ ሥልጣኖችን "**በምህረት**" ስለመልቀቁ ሊነግረንና ሊያስጮህ የፈለገው ዜና፣ በመሠረቱ እሱ በፈለገው መንገድ የሄደለት ባይሆንም ጉዳዩ ግን አነጋጋሪ መሆኑ ሐቅ ነው። እርግጥ ነው ያ አሠቃቂና ኢትዮጵያን እንደ ሃገር ጥቁር ከል ያለበሰው ቀዩ ሽበር በተነሣ ቁጥር፣ ድፍን አገሩንና ህዝብን ማነጋገሩ ደግሞ፣ የተገባ ነው - ሕዝብና "መንግሥት" ትናንትም ሆነ ዛሬ ገና አልታርቁምና ነው፤ የሕዝባችን ሰቆቃና እምባ በወጉ ገና አልታበሠም፣ አልደረቀም እና ነው። ያ አሠቃቂ ግፍ በሐገርና በህዝብ ላይ ጥሎ ያለፈው የሕሊና ቁስልና ያስከተለው መዘዝም እንዲሁ ቀላል አይደለም። ዛሬም ቢሆን ግን እንዲህ ዓይነቱ ሽብር በኢትዮጵያኖች ውስጥ ዕለት በዕለት እየተካሄደ ያለ ነገር በመሆኑ ጉዳዩን ይበልጥ ውስብስብ አድርጎታል።

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ!

ያ የትናንቱ የደርግ/ኢሠፓ ሽብር አዎ የብዙ ኢትዮጵያዊያንን ቤት አፍርሷል፤ ያ ሽብር እከሌ ከእከሌ ሳይል የሁሉንም ኢትዮጵያዊ በር አንኳኩቷል፣ በርግዶም ገብቷል፤ ያ ሽብር አዎን የኢትዮጵያዊያንን አንገት አስደፍቷል። ሽብሩ እስከአሁን ወደር አልተገኘለትም። ሰቆቃውን ይበልጥ ዘግናኝ የሚያደርገው ደግሞ እናት የልጇን እርም እንድትበላ የተደረገበትና በልጇ ሞት ላይ እንደትዘፈን የሆነበት አጋጣሚ መሆኑ ሲሆን ይህም የታሪካቸን ጥቁር ጠበሳ መሆኑ አልቀረም። ይህ ዕልቂት በሕዝብ ፊትና በዓለም አቀፍ የመገናኛ ተቋሞች ሳይቀሩ (በአደባባይና በአዋጅ የተከናወነ ነበርና) በመቅረጸ ድምፅና በመቅረፀ ምስል አስደግፈው በጊዜው ማጋለጣቸው አይዘነጋም። እርግጥ ነው የዚያን ጊዜው የሽብር ሠይፍ የተሳለው "**በኢትዮጵያ ትቅደም**" አዋጅ ተጀቡኖ ኢትዮጵያዊያን በኢትዮጵያዊያን የተቀሉበትና የተፈጁበት እንደነበር ታሪክ የሚያስታውሰው ነው። ደም እንደ ጎርፍ ፈሠሠ። ወላጆች ልጆቻቸውን ተነጠቁ። አንድ እናት አንድ ልጇን፤ ከአንድ ቤተሰብ ውሰጥ በትንሹ 2 እና 3 ልጆቻቸውን ያጡ እናቶች ቁጥራቸው የትየለሌ ነው። የስንቱስ ቤት ነው የፈረሰው....? ይሄ መራራው ሐቅ ነው። ስለዚያ ሽብር ገና በቅጡ አልተነገረም። ዛሬ ስለትናንትናው ሽብር 20 ዓመት እያቅራራ ባንጻሩ በጉልበቱ የህዝብን ሥልጣን ነጥቆ ቤተ መንግሥት ውስጥ የመሸገው መንደርተኛው ወያኔ፣ ይህንን የቀይ ሽብር ጉዳይ እያነሳ በመጣል ዳኛም፣ ምሕረት ሰጭና ነሽ ሆኖ ለመታየት መፈልጉ፣ አገዛዙ ምንኛ በጭንቅት ላይ እንዳለ አመላካች ነው። እርሱም ቢሆን እንደ ቢጤው በጉልበት መጥቶ በሽብር ሥልጣኑን ለማቆየት የሚፍጨረጨር ነውና አዎን የትናንቱ ሽብር እንደዛሬው ወያኔዊው ሽብር በጎጥ ሠይፍ አልተሞረደም እንጅ፣ የሁለቱም አገዛዞች የሽብር ምንጭ የሚቀዳው ከአምባገነንነት የጭካኔ አንጎል ለመሆኑ አያጠያይቅም። ደርግ/ኢሠፓ "**እናት አገር ወይ ሞት**" በሚል አዋጅ ላይ ቆሞ ያን መሰል ሽብር ማካሄዱን "**ኢትዮጵያን በመውደድ**" አስመስሎ ሊስለው ሞክሯል። ይሄንን የመንግሥቱን የጭካኔ ሥዕል አንዳንዶች አውቀውም ሆነ ሳይውቁ እንዳለ በመውሰድ፣ ዛሬ መንደርተኛው የወያኔው አሸባሪ አገዛዝ የሚያካሄደውን ሰቆቃ የተለዩ በማስመሠል፣ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ቢያንሥ "**ኢትዮጵያን ይወድ ነበር**" እያሉ ሰውዬውን ከፀፀቱ እንዳይፃዳ ሊያሞካሹት ይዳዳሉ። የወያኔ አገዛዝም "**ትግራይ እስክትለማ ሌላው አገር ይድማ**" በሚል ኋላ ቀር የጎጥ አስተሳሰቡ ላይ ቆሞ በ"**አንቀፅ 39 ሕገ-ወያኔ**" አዋጅ ላይ በመጎዝጎዝ ነው ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ሊያጠፋ፣ እሣት ጎርሶ ተስሎና ተደግሶ መምጣቱን ያበሰረው። የለገሠ ዜናዊው የወያኔ አገዛዝ ከመንግሥቱው የኢሠፓ አገዛዝ የሚለየው፣ ምናልባት የዜናዊ ልጅ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ስለመምጣቱ በአደባባይና በአዋጅ እየተናገረ መምጣቱ ብቻ ነው። ባቢሌ ቶላ እንዲህ ዓይነቱ ሽብር በማንኛውም ሥርዓትና አገዛዝ ሊወለድ እንደሚችል በመፅሐፉ ላይ እንዲህ ሲል አስጠንቅቆ ነበር።

"ደጋግመን እንደገለፅነው ቀይ ሽበር በማንኛውም ሥርዓት ሊወለድ የሚችል በመሆኑ፣ የመፅሐፉ ዋንኛ ዓለማ ይህ ቅፅፈት/እርግማን ዳግም እንዳይወለድ ለማድረግ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ነቅቶ  የበኩሉን አሥተዋጽዖ ማድረግ እንዳለበት ለመጠቆምና ለማሳሰብ ነበር/ነውም " **ይላል**

ይህንን ከላይ የተቀመጠውን የባቢሌ ቶላ ምክር፣ ያኔ ስንቶቻችን እንሆን ልብ ብለን የወሠድነው? በመሠረቱ ያ አስከፊና አሠቃቂ የሆነው ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ ሲካሄድ፣ ሽብሩ በእርግጠኝነት ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ግልፅና ግልፅ ነው፣ የሽብሩ ዋና ዒላማ ለሟቾቹ ሳይሆን ቋሚው እንዲርድና ህዝብና ሀገርም ለአምባገነኖች ፀጥ፣ ለጥ ብለው እንዲገዙ በዕቅድና በአዋጅ ሆን ተብሎ የተደረገ ለመሆኑ ዋቢ መጥቀስ አይስፈልግም። ይሁንና አሁን ሥልጣን ላይ ያለው የወያኔ/ሕውኃት አገዛዝና የአገዛዙ ፈለጭ ቆራጭ የሆነው ለገሠ ዜናዊ በዚያ መንሱት ወቅት ቀዩን ሽበር ሲያካሂድ ከነበረው አገዛዝ ጋር፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሽብሩ ተካፋይ እንዳልነበረ ሁሉ፣ ዛሬ ያንን ሽብር እታደጋለሁ እያለ ሲውረገረግ መታየቱ፣ እጅግም የበደል በደል ነው። ስለ እውነት ግን ሃቅ መነገር ካለበት እንዲህ ዓይነቱን የጭካኔ ድርጊት በተጨማሪ አሳዛኝና ሰቅጣጭ የሚያደርገው፣ በዚያን ዘመኑ ሽብር ሆነ አሁንም በሚካሄደው ሽብር ዋና ተጠቂ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብና የሽበሩ ዋና ሰለባ የሆነው ኢሕአፓ፣ በትናንትናው አገዛዝም ሆነ በዛሬው አገዛዝ የሚታደኑ፣ የሚታሠሩ፣ የሚሳደዱና የሚገደሉ፣ መሆናቸው ነው። ኢሕአፓን በተለይ ደግሞ እንደድርጅት ዛሬም ጠላት አድርጎ ሊያጠፋው የሚቅነዘነዘው ወያኔ፣ የዚህ ሰቅጣጭ ድራማ ተዋናኝ ሆኖ ልታይ፣ ልታይ ማለቱ ምን ዓይነት የጭካኔ ሠብእና እንደተላበሰ የሚያሳይ ነው።  ያ የትናንቱ  ሽብር የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ወላጅ እናትና አባት ቅስም የሠበረ፣ እናት በልጆቿ ሬሣ  ላይ፥

አቤት ደስ ማለቱ፣ ደስ ማለቱ፤
"አናርኪስት" ተገድሎ፣ ማየቱ።
አቤት ደስ ማለቱ ፣ ደስ ማለቱ፣
"የአናርኪስትን" ሞት መመልከቱ።

ብላ እንድትዘፈን የተደረገበት፣ ልጆቿ መገደላቸው አንሶ ለተገደሉበት የጥይት ዋጋ ከፍላ፣ ሬሣ እንድትገዛ የተጠየቀችበት አሠቃቂ፣ ህዝብን ያሸበረና ያስደነበረ ድርጊት እንደነበር ታሪክ መዝግቦታል። በአጠቃላይ ያ ሽብር የሰው ልኩ የተፈተነበት፣ የሰው ልጅ አውሬነቱ ወጥቶ የታየበት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። እርግጥ ነው ያኔ ያን መሳይ አሰቃቂ ዕልቂት ሲካሄድ ደግሞ በአርምሞ ተመልክተን በማለፋችን፣ ዛሬ ኢትዮጵያ ለገጠማት ችግርና ለተመሳሳይ ሽብር መዳረጓን አመላካች ከሆነው "**አንድ ትውልድ ለመምተር ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ** " ከባቢሌ ቶላ መፅሐፍ  ውስጥ ተጨማሪ ለአብነት እጠቅሳለሁ፥

ቀዩ ሽብር በፋሽስቱ መንግሥት (ደርግ/ኢሠፓ) ቢካሄድም በሂደቱ ተሳታፊው፣ ለጉዳቱ ተጠያቂው በእሱ ብቻ የሚወሰን አልነበረም። በወቅቱ የጠቆመ፣ ያጋለጠ፣ ጎረቤቱ፣ ወገኑ ሲረሸን አላየሁም ያለው፣ ወጣቱ በጠራራ ፀሐይ ሲደፋ ፀጥ ያለ፣ ለአምባገነኑ አረመኔው ሥርዓት ያጎበደደ ወዘተ.... ሁሉ  ራሱን መጠየቅ፣ ሕሊናውን  መመረመር ይገባዋል፤ ቀይ ሽብሩ የተሠነዘረው በሟቾቹ ላይ ሳይሆን በቀረውና በቋሚው ላይ ነበር።

ትክክል ነው። ባቢሌ ቶላ በመፅሐፉ ሊገልጠው እንደሞከረው ይህንን መሳይ አሠቃቂ ሽብር ተመሳሳይ የትውልድ ዕልቂት በኢትዮጵያ እንዳይደገም ለመከላከል ይረዳ ዘንድ ከተመክሮ ጋር አያይዞ ለማስጨበጥና ለማመላከት ነበር መፅሃፉን የጻፈውው፤ ዳሩ ግን  "ምክር የት ነው መገኛሽ ቢሏት .... ከደኃ አለች" እንደተባለው ሁሉ ይህንን መሰል ምክር ትናንትም እንዳልሰማን ሆነን፣ ዛሬም እንዳለዩን አድርገን ማለፉን ስለመረጠን፣ እነሆ ዛሬም በወያኔው የሽብር እሣት መለብለቡን የቀን ተቀን ኑሮአችን ለማድረግ ተገደናል። አዎ ትናንት ያን መሣይ ሽብር ልክ አይደለም ብለን አብረን አውግዘን በነበረ፣ አሁን ለጠበቀን ለዛሬው ወያኔያዊ ሽብር ባልተዳረግን ነበር።

ወያኔ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ 20 ዓመት ወያኔያዊ ሽብር ሲያካሄድ የቆየውና፣ ሽብሩን የሚያካሄደው ደግሞ ከደርግ/ኢሠፓ አገዛዝ በተበዳራቸው ወይም በወረሳቸው ሰዎች አማካኝነትና አማካሪነት ጭምር መሆኑ እየታወቀ፣ ዛሬ 19 ዓመት አሥሮ ያቆያቸውን የደርግ ባለሥልጣኖች "**በምሕረት**" ልለቅ ነኝ ማለቱ ግን  እውነት ለእነርሱ  አስቦ..?  ወይስ ለራሱ ተጨንቆ ...?

የተከበራችሁ አንባቢዎች!

ዛሬ ለደርግ ባለ ሥልጣኖች **"ምሕረት"** ሰጭና ነሽ ሆኖ ያዙኝ ልቀቁኝ የሚለው መለሥ ይህንን ዓይነት የቸከ ደራማውን ለማጫወት ሲነሣ፣ እንደወትሮ ሁሉ እስቲ በዚህ ደግሞ የፖለቲካ ጢብ ጢብ ልጫወትባቸው ብሎ ሳይሆን፣ ከምሩ የመንግሥቱ ኃ/ማርያም እጣ ፈንታ እርሱም ላይ እንደደረሰና እንደተቃረበ ሰለሚያውቅ ነው። መለሥ ዜናዊ እስካሁን ሥልጣኑን እየጠበቀ ያለው በጥንካሬው ሳይሆን ፍርኃቱ በሚወልደው ጭንቀቱ ነውና ይህንን ለማወቅ የመንግሥቱ ኃ/ማርያምን መፅሐፍ መጠበቅ የለብንም። ያማ ባይሆን 99.6% አሸንፍኩ የሚለው ሰው 20 ዓመት "እገዛዋለሁ" የሚለውን ህዝብ ተደብቆና ፈርቶ ራሱን በመሣሪያ አጥር ሊሸሽግ ባልበቃ ነበር። ለዚህም ነው ይሄንን የታመቀ የህዝብ ሰሜት ለማውቅና ለማስተንፈስ ወያኔ ይሄንን የቀይ ሽብር ጉዳይ በየጊዜው ባነሣ ቁጥር ሁልጊዜ ከህዝብ ከባድ ተቃውሞ ሲገጥመው ቢታይም የሰሞኑ የደርግ ባለሥልጣኖችን **በ"ምሕረት"** እለቃለሁ የሚለው ዜና ግን ከራሱ የውሰጥ ሰዎች ሳይቀር ከባድ ተቃውሞ እንደገጠመው ዓይጋን መመልከቱ ብቻ ይበቃል።

በነገራችን ላይ አምባገነኖች ከአንድ ምንጭ ነው የሚፈልቁትና እንደ ታላቅ ወንድሙ መንግሥቱ ኃ/ማርያም በሥልጣኑ የሚመጣበትን ማንኛውንም ሰው ከጫካ ጀምሮ እያጠፋ የመጣ ነውና፣ ሥልጣኑን ይጠብቁለት ዘንድ ለዕለት ጉርስ የሚከፍላቸውን ካድሬዎችንም ህዝብን እያስራበም ቢሆን ደሞዝ ከፍሎ ማስጮህ ግዴታው ነው።

ሀገርን በጎጥ ሸንሽኖ በዘር ማጥፋት ወንጀል መላ አካላቱ በደም የተነከረውና የሰው ነፍስ በጅምላ እየጨፈጨፈ ወደ ጉድጉዳ የሚወረውረው ጎጠኛና አሸባሪው አገዛዝ ዋና ቁንጮ ለገሥ ዜናዊ፣ እንዲህ ዓይነት ሰቆቃ እየፈፀመና የሐገሪቱን ኃብት እየዘረፈና/ ዘርፎ በሠላም እኖራለሁ፣ በምህረት ወይ በይቅርታ ነፃ እወጣለሁ ብሎ የሚያስብ ከሆነ መቼስ ማልጎደኒ እያልኩ፣ ሰውየው ራሱ **'ማለም ይቻላል'** ብሏልና ማለሙንና መቃዥቱን አይከለከልም። ዛሬ መንግሥትና ህግ በሌለባት ሀገረ ኢትዮጵያ እነ ስዬ ህዝብን እንኳ ይቅርታ ለመጠየቅ በዕብሪት ተነፍተው "በነፃ" ሲጎማለሉ ግዜ መለስም እውነት መሰሎት፣ እኔም አንድ ቀን እንዲህ መዋረዴ አይቀረምና እስቲ ይሄንን ህዝብ ልፈትሸው ብሎ፣ ዛሬ የደርግ ባለ ሥልጣናትን **"በምህረት"** እለቃለሁ ብሎ ያስጮኸው ጥይት በራሱ ላይ ባርቆ ራሱን መልሶ ሊያቆስለው ችሏል።

የሚገርመው መንግሥቱ ኃ/ማርያም ራሱም እስካሁን ድረስ እንኳን ሰው ዝምብም አልገደልኩም ሲል ከርሞ፣ አሁን ደግሞ **"መንግሥቱ በፈቃዳቸው ለፍርድ ለመቅረብ ዝግጁ ናቸው"** የሚል ዜና በአማላጅ ሊያስነግረን ቢከጅለም ነገር ግን እኔን የሚፈርደኝ ወያኔ ሳይሆን ህዝቡ ነው ማለቱ ደግሞ ፈገግ ማስድረጉ አልቀረም። ይህ ነፍሰ ገዳይ ግለሰብ ዛሬ እንደሚለው በህዝብ እንዲዳኝ ኢትዮጵያን ለህዝባዊ መንግሥት አመቻችቶ የሄደ ይመስል፣ ዛሬ ደርሶ እንዲህ ለማለት መደፈሩ ዛሬም ይህ ሰው ከበሽታው እንዳልተፈወሰ አመላካች ነው። ትናንትና ሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት ይሄንን የሕዝብ መንግሥት እንዲቋቋም ጥያቄውን አንስተው በታገሉ ወጣቶች ላይ ፍጅትን መረጦ፣ በወጣቶች ላይ የቀይ ሽብሩን አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ አስደግፎ ሲያወጣ እንዲህ ዓይነቱ በህዝብ የሚዳኝ ሥርዓት እንዳይፈጠር በመፈልጉ ነበር። በመጨረሻም እንደ ቴዎድሮስ አንድ ጥይት እስኪቀረኝ ድረስ እያለ ሲደነፋ ቆይቶ፣ ሃገሪቱንና ህዝቡን ለወያኔ አሳልፎ ሰጥቶ ሄዷል። ታዲያ ዛሬ ያልዘራውን ሊያጭድ መመኘቱ በእጅጉ አሳፋሪ ነው።

በዓለም ላይ እንዲህ ዓይነት ነፍሰ ገዳዮች፣ ዛሬ ባይሆን ነገ፣ ነገ ባይሆን ከነገ ወዲያ ከያሉበት እየታደኑ ወደ ፍትህ አደባባይ መቅረባቸው አይቀሬ መሆኑ፣ በዓለም ላይ በህይወት አለሁ የሚል ሰው ሁሉ ሊስተው አይችልም። ዓለም እንዲህ ዓይነት ነፍሰ ገዳዮችን ስትፋረድ በዓይናችን እያየን ነውና! በሂትለር ጊዜ ህዝብ በመጨፍጨፍ የተባበሩ ሰዎች እያንዳንዳቸው በዓለም ላይ እተደበቁበት እየታደኑ ለፍረድ መቅረባቸው እስከአሁን አላቋረጠም። ሕዝብን ጨፍጭፎ የሠላም እንቅልፍ ተኝቶ ማደር አይገኝምና ነው። ለመማር የሚፈልግ ከታሪከም መማር ይቻል ነበር። አምባገነኖች ግን በሰው ነፍስና በሰው ደም የሠከሩ ናችውና፣ መጀመሪያውኑ አዕምሮአዊ ጤንነታቸው አጠያያቂ ነው። ለዚህም ነው የኛዎቹም ነፍሰ ገዳዮች ላደረሱት ወንጀል ሳይፀፀቱ፣ ለፈፀሙትና እንደ ጎርፍ ላፈሰሱትና ለሚያፈሱት የሰው ደምም አንዳችውም ቢሆኑ ኃላፊነቱን ለመውሰድ ሲቸገሩ የምናያቸው። መንግስቱ ኃ/ማርያም ሆነ ለገሠ ዜናዊ የሰው ነፍስ እንደ ዝምብ ቆጣሪዎች ናችውና ላጠፉት የሰው ነፍስ ሁሉ፣ ራሳቸውን ያዳኑ እየመሠላቸው ዝምብም አልገደልንም ማለትን ይወዳሉ፣ አልፈው ተርፈውም ሠላማዊ ሰዎች ሆነው ለመታየትና ለመቅረብ ይንደፋደፋሉ። እጅግም ፈሪዎች በመሆናቸው ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮኃል እንደሚባለው ከተበዳዩ በላይ ራሳቸው እንደቆሰለ አውሬ ጣራ እስኪቀደድ ደረስ ያዞ እምባ በማባት ይጮኃሉ። ከተቻላቸውም ለወንጀላቸው ማጠየቂያና ወንጀላቸውን በሌላው ላይ ለማላከክ፣ ሌላ ሰው ሁሉ

አሻግረው ሲፈልጉ የምናያቸውና የምናዳምጣቸው ለዚህ ነው። አንዱ በአንዱ ላይ እያሳበበ ሁሉም ነፍሰ ገዳይ ራሱን "ነፃ" ሊያደርግ ይሟሟታል - ሙት ይዞ ይሞታል እንደሚባለው። እንደእነዚህ ዓይነቶቹ እንሥሣዋ አለች እንደተባለው አስተሳሰብ የሚያስቡ ዓይነት ሰዎችን ይመለከታል። ምን ነበር አለች የተባለችው እንሥሣዋ "እኔ ከሞትኩ ሥርዶ አይብቀል..."! አይደል። እንዲያው ለነገሩ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ለመሆኑ፣ ልጆቻቸውን ይወዳሉን...? የሚወዷቸው ቢሆንማ ይሄን ሁሉ የሠሩትን ግፍና በደል ተሸከመው ለልጆቻቸው የሚያስተላልፉት ባልሆነ ነበር። መጥኔ ለልጆቻቸው! ልጆቻቸው በእጅጉ ያሳዝኑኛል።

ወያኔ እራሱ እነፀጋዬ ደብተራውን አፍኖ ወስዶ የት እንዳደረሳቸው ባልታውቀባት ኢትዮጵያ፣ ዛሬ ለገሠ ዜናዊ "ምሕረት ሰጪ" ሆኖ ያዞኝ ልቀቁኝ ማለቱስ ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው? እነአበራሽ በርታ፣ በርሄ፣ አምሃ በለጠ፣ ስጦታው ሁሴን፣ አሉላ፣ ተስፋዬ ከበደ(አቡሃይ)፣ ወንዱ ሲራክ፣ አበራ(ቀይ ዘብ)፣ ለማ ኃይሉን፣...ወዘተ የት እንደገቡና ፍትህ እንዲያገኙ ያልጠየቀች የዛሬዋ ኢትዮጵያ፣ የትናንትና ወንጀለኞችን "በምህረት" ልለቅ ነኝ ብላ አዋጅ ማስነገሯን የማይጠይቅ ኢትዮጵያዊ/ዊት፣ ዛሬ ዛሬ ጭንቀቴ ለኢትዮጵያና ለህዝቧ ነው ብሎ/ብላ፣ ቢያወራልኝ/ብታወራልኝ፣ ጆሮየን አላውስም ብለው/ ብላት መኑ ላይ ነው ኃጢያቴ? እረ እየተሠተዋል!

የሕዝብ ትግል ያቸንፋል! የታሰሩ የፐለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላም ትኑር
ቸር ይገጠመን
january 2/2011